# የቃላት ኢኮኖሚ

ታደሰ ብሩ

ቃላት ያለአግባብ ሲባክኑ አያሳዝናችሁም? አንድ ገጽ ሙሉ አንብባችሁ ምንም ፍሬ-ሃሳብ ሳታገኙ ስትቀሩ ምን ይሰማችኋል?

የመምህርነት ሙያዬ ቃላት በጥበብ የተደረደሩበትና በውበት የተሞሉ ጽሁፎችን የማንበብ እድል ሰጥቶኛል። በዚያው መጠን ደግሞ "ከሜዳ ታፍሰው በተበተኑ" ቃላት የተሞሉ ጽሁፎችን እንዳነብ አስገድዶኛል። መልዕክቱ ምንም ይሁን ምን የመጀመሪያ ዓይነቶቹን ጽሁፍ ማንበብ ያስደስታል። የሁለተኛዎቹን ዓይነት ጽሁፍ ከማንበብ ግን "ምናለ የጉልበት ሥራ በሠራሁ" ያሰኛል። ልዩነቱ የዚያን ያህል ነው።

አሳክቶና አስውቦ መፃፍ የኪነ ጥበብ ችሎታ ቢሆንም ከአስተሳሰብ ጥራት ጋር ይያዛል የሚል እምነት አለኝ። ቋንቋ የአስተሳሰባችን ስነ አመክኖ መግለጫ ነው።

አቶ ቀመሩ ደሳለኝ "ከሃዲዎችና ባንዳዎች የኢትዮጵያን አኩሪ ታሪክና አንድነት ሊያንኳስሱትና ሊቀይሩት አይችሉም"[1] በሚል ርዕስ የፃፉትን በምሳሌነት ብጠቀም ቅር እንደማይላቸው ተስፋ አደርጋለሁ።

የጽሁፋቸው የመጀመሪያ አንቀጽ የሚከተለው ነው።

> የኛ ቀደምት ትውልዶች ትውልድን ሊቀርጹና ሊያንጹ የሚችሉ ቁም ነገሮችን አውርሰው ያለፉ፣ የዜግነት ግዴታቸውን በሙሉ የተወጡ አኩሪ ታሪክ ያተረፉ እንጂ እንደነ አቶ አንዳርጋቸው (በትናቸው) ፅጌ ግንቦት 7 ጰያፍ አነጋገር አሳፋሪ ታሪክ አልተውልንም። አለኝታና መመኪያ ኢትዮጵያዊነትን አውርሰውናል። አዎ! እውነት ነው! ኢትዮጵያዊነትን ከወላጆቹም ሆነ ከኅብረተሰቡ ያልተማረ ትውልድ እንዴት ኢትዮጵያዊ ይሁን !!

ይህ በሁለት ዓረፍተ ነገሮች የተገነባ አንቀጽ ነው (ሁለተኛው ዓረፍተ ነገር የሚመስለው የመጀመሪያው ቁራጭ ስለሆነ እንደ አንድ አንቧቸው)። የመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር ረዥም፣ ውስብስብና ጫጊ በመሆኑ ሃሳቡን መረዳት ያስቸግራል። ተቸግራችሁም ቢሆን የተረዳችሁት ሃሳብ ካለ ሁለተኛው ዓረፍተ ነገር ያፈርሰዋል።

እስቲ የፀሃፊው ሃሳብ ለመረዳት እንሞክር።

1. የመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር መልዕክት "ቀደምት ትውልዶች መልካም ነገሮችን ብቻ ትተው አልፈዋል" የሚል ይመስለኛል። አንዳርጋቸውም ሆነ በትናቸው ጽጌ የገባው በምሳሌነት እንጂ

[1] ጽሁፉን እዚህ ያገኙታል http://www.assimba.org/Articles/Kehadiwoch-11.pdf

የመልዕክቱ ባለቤት አይደለም። “ግንቦት 7” ደግሞ ምን እንደሆነ ፈጽሞ ግልጽ አይደለም። እንዲያውም እንግዳ አንባቢ ይህንን ጽሁፍ ሲያነብ የአቶ አንዳርጋቸው አያት “ግንቦት”፤ ቅድመ አያቱ ደግሞ “7” ሊመስለው ይችላል።

2. የሁለተኛው ዓረፍተ ነገር ጭብጥ “አሁን ያለው ትውልድ ከወላጆቹም ሆነ ከኀብረተሰቡ ባለመማሩ ኢትዮጵያዊ መሆን አልቻለም” የሚል ነው።

ሁለቱም ዓረፍተ ነገሮች የሚያወሩት ስለትውልድ ነው። ለየብቻቸው ሲነበቡ ከላይ የጠቀስኩትን መልዕክት ይሰጣሉ። ሁለቱም በአንድነት ሲነበቡ የሚሰጡት መልዕክት ግን ምን እንደሆነ ለኔ ግልጽ አይደለም። የዚህን አንቀጽ መልዕክት ለመረዳት የተጨነቀ ሰው ከሚከተሉት ሁለቱ አንዱ መያዙ አይቀርም።

*የቀድሞው ትውልድ መልካም ነገሮችን ብቻ ሰርቶ ያለፈ ቢሆንም የአሁኑ ትውልድ ኢትዮጵያዊነትን ከወላጆቹም ሆነ ከኀብረተሰቡ አልተማረም።*

*ወይም*

*የቀድሞው ትውልድ መልካም ነገሮችን ብቻ ሰርቶ ያለፈ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያዊ የለም።*

ፀሃፊው ለማስተላለፍ የፈለጉት መልዕክት ግን ከላይ ከሰፈሩት ውስጥ ማናቸውንም እንዳልሆነ መረዳት ቀላል ነው። ከአርዕስቱ ተነስተን ፀሃፊው ለመፃፍ የፈለጉት ብንገምት እና የፃፉት ስናነብ ለየቅል ናቸው።

ፍልስፍና የሚመስለውን ይህንን አንቀጽ ደግሞ ልብ በሉልኝ

**ፖለቲካ በሳይንስነት አንፃር ካልታዬና ካልተቀረበ በስተቀር መፎከሪያ ብቻ ሆኖ ይቀራል። ችግርን፣ የራስን ሚና መረዳት አለመቻል፣ የማሰብ ኃይልንና እውቀትን ከታሪካዊ ግንዛቤ ጋር አጣጥሞና ተጠቅሞ በግልጽ የሚታዩ ችግሮችን ለማስወገድ አለመጣርና በራስ ክልል ብቻ እየተሽከረከሩ ማውራትና ከእውነት እየሸሹ መኖር ችግሮችን ያባብሳል፣ መፍትሔ እንዳይገኝለት እንቅፋት ይሆናል። ጠለቅ ብሎ ለአገር ወገን አንድነት ማሰብ መቻል፣ ጥናት ማድረግና መወያየት ብልህነት የተሞላበት መፍትሄ ነው።**

ይህ አንቀጽ አንዳች ቁምነገር ሊነግረን የተዘጋጀ መስሎ አጓጉቶን ምንም ሳይል ይጠፋል።

ለመሆኑ አንቀጹ የሚያወራው ስለ ፓለቲካ ነው ወይም ስለ ፓለቲካ ሳይንስ፤ ወይስ ስለ ችግሮች አፈታት? የአንቀጹ መልዕክት ምንድነው?

የመጨረሻውን ዓረፍተ ነገር በጥንቃቄ አንብቡት። ማሰብ፣ ጥናት ማድረግና መወያየት ወደ መፍትሄ ያደርሱን ይሆናል እንጂ ራሳቸው እንዴት መፍትሄ ይሆናሉ? ደግሞስ መፍትሄነታቸው ለየትኛው ችግር ነው?

በአጠቃላይ ይኸ አንቀጽ በአርዕስቱ ከተነገረን ጉዳይ - ማለትም “ከከሃዲዎችና ባንዳዎች ...” ጋር ያለው ግኑኝነት ምንድነው?

በጽሁፉ ስለኢትዮጵያ ታላቅነት በሰፋት ተዘርዝሯል። አቶ አንዳርጋቸው (በትናቸው) ጽጌ፣ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋና ዶ/ር ጌታቸው በጋሻው በየመሃሉ በከሃዲነትና በባንዳነት ሲሰደቡ እናነባለን እንጂ የሚሰደቡበት ምክንያት አልተገፀም።

ለኢትዮጵያ ፓለቲካ እንግዳ የሆነ ሰው ይህንን ጽሁፍ አንብበህ የነአቶ አንዳርጋቸው ወንጀል ምን ሊሆን እንደሚችል ገምት ቢባል “ *‘ኢትዮጵያ በመጽሃፍ ቅዱስ፣ በቅዱስ ቁርዓንና በሌሎች የሃይማኖት መፃፍሀት ላይ ተደጋግማ አልተጠቀሰችም፤ እነ ሆሜር፣ ጊቤንስና ሂሮዶተስ ስለኢትዮጵያ ታላቅነትና ስመ ጥሩነት በአክብሮት በስፋት አላተቱም’ በማለታቸው መሆን አለበት”* የሚል ድምዳሜ ላይ ሊደርስ ይችላል። ፀሃፊው ግን ይህንን መልዕክት ለማስተላለፍ ሲሉ የፃፉት አይመስለኝም።

ባጭሩ ጽሁፉ ግልጽ አይደለም፤ በግድ እንረዳህ ከተባለም ጽሁፉ የሚለው ጸሃፊው ለማለት የፈለጉትን አይደለም። ጥሩም መጥፎም ቃላት በዘፈቀደ ተሸጓጉጠዋል።

የአቶ ቀመሩ ደሳለኝን ጽሁፍ ያነሳሁት እንዴት መፃፍ እንደሌለብን ለራሴም ለሌላውም ወገኔ ትምህርት እንዲሆነን በማስረጃነት ለመጠቀም እንጂ በጽሁፉ ይዘት ላይ የምሰጠው አስተያየት ኑሮኝ አይደለም። ፀሃፊው ሊያስተላልፉት የሚፈልጉት መልዕክት ያላቸው ከሆነ ገና አልፃፉትምና ደግመው ተጠንቅቀው ይፃፉት።

ዋናው መልዕክቴ የሚከተለው ነው፡-

> *ጽሁፋችን ሃሳባችንን በትክክል መግለጽ መቻሉን እናረጋግጥ። አላስፈላጊ ቃላት ማጎር ከማደናገር ሌላ የሚፈይደው ነገር የለም። ቃላት ሃብት ናቸው፤ በአግባቡ እንጠቀምባቸው[2]።*

አመሰግናለሁ።

[2] . ይችን ደግሞ ላንሳ። ጽሁፉ “የተገንጣይና የአለቅላቂዎቻቸው ሴራ ይከስማል!!” በሚል መፈክር ይጨርሳል። ለመሆኑ “አለቅላቂ” ምን ማለት ነው? በመውደም ፋንታ ለምንድነው የሚከስሙት?